ኛ ዓመት ቁጥር 2
6th Year N° 2

ባህር ዳር መስከረም 22 ቀን 1993 ዓ.ም
Bahir Dar 2nd Day of October/2000

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት

ዝክረ ህግ
ZIKRE HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 3.00	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ተጠባቂነት የወጣ	ፖ.ሣ.ቁ 312 P.O.Box

ማውጫ	CONTENTS
አዋጅ ቁጥር 51/1993 ዓ.ም ሁለተኛው የአማራ ብሔራዊ ክልል ህገ መንግሥት ማሻሻያ አዋጅ ገፅ 4	Proclamation N°51/2000 A Proclamation To Provide For The Second Amendment Of The Constitution Of Amhara National Region Page 4

አዋጅ ቁጥር 51/1993 ዓ.ም
ሁለተኛው የአማራ ብሔራዊ ክልል ህገ መንግሥት ማሻሻያ አዋጅ

በተጠናቀቀው የመጀመሪያ ዙር የአምስት ዓመታት መርሀ ግብር ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ በሂደት የተከሰቱትን ችግሮች አለመገድ የክልሉን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ዕድገት ይበልጥ የሚያፋጥን ህገመንግሥታዊ ሁኔታን መፍጠር በማስፈለጉ፣

ከዚህም የተነሣ ግልፅነት የሚጐድላቸውንና ሙሉ ተፈፃሚነቱ አመች ሆነው ያልተገኙትን አንዳንድ የህገ መንግስቱን አንቀጾች መርምሮ አንደገና ማሻሻል ተገቢና ወቅታዊ ሆኖ በመገኙቱ፣

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት በህገመንግሥቱ አንቀጽ 100 ላይ የብሔራዊ ክልሉን

Proclamation N° 51/2000
A Proclamation To Provide For The Second Amendment Of The Constitution Of Amhara National Region

Where as, it has been essential to create a favorable constitutional environment which would facilitate the overall socio-economic and political transformation of the regional state by doing away with all embracing difficulties that have been observed during the course of our exercise in the just completed first five-years' development plan;

Where as, as a result, it has become imperative and timely to select and revise for possible examination and amendment of those articles of the constitution which lack clarity and pose obscurity because of which full implementation of the same remains doubtful;

Now, therefore, the council of the Amhara National Regional state in accordance with the powers

388

388

ህገመንግሥት ለማሻሻል በተሠጠው ሥልጣን መሠረት ከዚህ የሚከተለውን አውጇል::

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ " ሁለተኛው የአብክ ህገመንግሥት ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 51/1993 ዓ.ም " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2. ማሻሻያ

በአዋጅ ቁጥር 2/1988 ዓ.ም የተቋቋመው የአማራ ብሔራዊ ክልል ህገ መንግሥት /እንደተሻሻለ/ በተጨማሪ በዚህ አዋጅ እንደሚከተለው ተሻሽሏል::

ሀ.የህገ መንግሥቱ አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/11/ እንደሚከተለው ተሻሽሏል::

11.በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት የክልሉን ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ ዋና አዲተርና ምክትል ዋና አዲተር ይሾማል::

ለ.የህገመንግሥቱ አንቀጽ 53 ንዑስ አንቀጽ 4 ተሻሽሎ እንደሚከተለው ተሰተካክሏል::

4.የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ቁጥር ከ13-17 ይሆናል::

ሐ.የህገ - መንግሥቱ አንቀጽ 56 ንዑስ አንቀጽ 1 እንደሚከተለው ተሻሽሏል::

1.ርዕሰ መስተዳድሩ የክልሉ ምክር ቤት ሊቀመንበር፣ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሰብሳቢና የመስተዳድሩ ሥራ መሪ ነው::

መ. ህገ መንግሥቱ አንቀጽ 56 ንዑስ አንቀጽ 4 እንደሚከተለው ተሻሽሎ ተሰተካክሏል::

4.የክለሉን ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት፣ምክትል ፕሬዚዳንት፣ ዋና አዲተርና ምክትል ዋና አዲተር መርጦ ለም/ቤቱ በማቅረብ ሹመታቸውን ያሰፀድቃል::

ሠ.የህገ መንግሥቱ አንቀጽ 65 ንዑስ አንቀጽ 1/1/ ፊደል ተራ ቁጥር /ሐ/ ተሠርዞ ከዚህ በታች በሠፈሩት ሁለት አዳዲስ ንዑሳን አንቀጾች ከተከፋፈለ በኋላ ቀሪው ድንጋጌ ፊደል ተራ ቁጥር /ሠ/ በመሆን ተሰተካክሏል::

ሐ. የክልሉ ፍትህ ቢሮ ኃላፊ
መ. የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽነር

ረ.የህገ መንግሥቱ አንቀጽ 69 ንዑስ አንቀጽ 3 ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 3 ተተክቷል::

3.የዞን መስተዳድር ሊቀመንበር፣ምክትል ሊቀመንበርና ዋሕፊ ከክልሉ ምክር ቤት አባላት መካከል በክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አማካኝነት ይመረጣሉ:: ሹመታቸውም ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ ይፀድቃል::

ሰ. የህገ መንግሥቱ አንቀጽ 69 ንዑስ አንቀጽ 4 ተሠርዞ

vested in it to amend the constitution under article 100 of the National Regional Constitution here by proclaims as follows.

1. short title

This proclamation may be cited as "The second Amhara National Regional State constitutional amendment proclamation N° 51/2000."

2. Amendment

The constitution of the Amhara National Regional State established by proclamation N° 2/1995 as (amended) is further amended as follows.

A. Sub article 3 (11) of article 49 of the constitution is amended as follows:

11.Appoint hereby the president and the vice president of the regional supreme-court as well as the auditor general and deputy auditor general of the region upon their presentation by the chief administrator.

B. Sub article 4 of article 53 of the constitution is hereby amended and re-formulated as follows.

4.The number of regional executive committee members shall run from 13-17.

C. Sub article 1 of article 56 of the constitution is hereby amended as follows.

1 . The chief administrator is the chairperson of the regional council and its executive committee as well as the managing head of the government.

D. Sub article 4 of article 56 of the constitution is hereby amended and reformulated as follow.

4. Select the president and vice president of the regional supreme court as well as the auditor general and deputy Auditor general and present same for their appointment and approval by the council.

E. Sub article 1(1) C of article 65 of the constitution is hereby deleted and subdivided into the following two new sub- Articles stipulated bellow after which the remaining provision is as consequence lettered (E).

C. Head of the Regional Justice Bureau
D. Commissioner of the regional police

F. Sub article 3 of article 69 of the constitution is hereby deleted and replaced by the following new sub article 3.

3. The regional executive committee shall elect the chairperson, the vice-chairperson, and the secretary of zonal administration out of the members of the regional council. Their appointment shall thus be submitted to and approved by the regional council.

G. Sub article 4 of article 69 of the constitution is

389

389

በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 4 ተተክቷል።

4. ሌሎች የዞን መስተዳድር አባላትም ከክልሉ ም/ቤት አባላት መካከል በክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተመርጠው ይሾማሉ።

ሸ.የሀገ - መንግሥቱ አንቀጽ 69 ንዑስ አንቀጽ 6 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 6 ተተክቷል።

6.ዞን ሥራ አስፈፃሚ አባላት ቁጥር ከ9-13 ይሆናል።

ቀ.የሀገ-መንግሥቱ አንቀጽ 73 ንዑስ አንቀጽ 1 ተሻሽሎ እንደሚከተለው ተሰተካክሏል።

1.የዞን መስተዳደር ሊቀመንበር ፣ የዞን ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሰብሳቢና የመስተዳድሩ ሥራ መሪ ነው ።

በ.የሀገ-መንግሥቱ አንቀጽ 76 ንዑስ አንቀጽ 2 ተሻሽሎ እንደሚከተለው ተሰተካክሏል።
2.ከም/ቤቱ አባላት መካከል ተመርጠ የሚቋቋምና ከ7-11 አባላት የሚኖሩት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ

ተ. የሀገ መንግሥቱ አንቀጽ 86 ንዑስ አንቀጽ 3 ተሻሽሎ እንደሚከተለው ተሰተካክሏል።
3.ተጠሪነታቸው እንደ አግባብነቱ ለመረጣቸው ህዝብ ለወረዳው እና/ወይም ለከተማው ምክር ቤትና ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ይሆናል፣

ቸ.የሀገ-መንግሥቱ አንቀጽ 87 ንዑስ አንቀጽ 1 ተሻሽሎ እንደሚከተለው ተሰተካክሏል።
1.እንደ አግባብነቱ የወረዳው እና/ወይም የከተማው ም/ቤትና ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሚያወጧቸውን ዕቅዶችና መመሪያዎች በሥራ ላይ ያውላል።

ኀ. የሀገ-መንግሥቱ አንቀጽ 89 ንዑስ አንቀጽ 2 ተሻሽሎ እንደሚከተለው ተሰተካክሏል።
2.የቀበሌው ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እንደአግባብነቱ ተጠሪነቱ ለመረጠው የቀበሌ ም/ቤትና ለሚመለከተው ወረዳ እና/ወይም ክተማ ም/ቤት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይሆናል።

ነ. የሀገ መንግሥቱ አንቀጽ 90 ንዑስ አንቀጽ 1 ተሻሽሎ እንደሚከተለው ተሰተካክሏል።

1.የቀበሌ ሊቀመንበር ተጠሪነቱ ለቀበሌው ም/ቤት ወይም ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው፣ ለታቀፈበት ወረዳ እና/ወይም ለከተማው ም/ቤት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይሆናል።

ኘ. የሀገ - መንግሥቱ አንቀጽ 90 ንዑስ አንቀጽ 5 እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

5.ለቀበሌው ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣ ለም/ቤቱ ለወረዳውና ወይም ለከተማው ም/ቤት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እንዲሁም ለኖረው ህዝብ በየጊዜው የሥራ ሪፖርት

hereby deleted and replaced by the following new sub article 4.

4.Other members of the zonal administration shall be elected out of the membership of the regional council and appointed by its execute committee.

H. sub article 6 of article 69 of the constitution is hereby deleted and replaced by the following new sub article 6;

6.The number of zonal executive committee members shall run from 9 to13.

I. Sub article 1 of article 73 of the constitution is hereby amended and reformulated as follows.

1.The chairperson of zonal administration is the head of zonal executive committee, not to mention that he/she is also in charge of its day to day administration.

J. Sub article 2 of article 76 of the constitution is hereby amended and reformulated as follows.

2. An executive committee elected and established from among the membership of the council having members Ranging from 7-11;

K. Sub article 3 of article 86 of the constitution is hereby amended and reformulated as follows:-

3.They shall be accountable, as the case may be appropriate, to the electorate, the woreda and or the urban council and its executive committee;

L. Sub article 1 of article 87 of the constitution is hereby amended and reformulated as follows;

1. Implements those plans and directives issued by the woreda and or the urban council as well as its executive committee, which ever may be appropriate there with.

M. sub article 2 of article 89 of the constitution is hereby amended and reformulated as follows;

2. The executive committee of the Kebele shall be accountable to its electing Keble council and the concerned woreda and or the urban council's executive committee, which ever may be appropriate under the circumstances.

N. sub article 1 of article 90 of the constitution is hereby amended and reformulated as follows;

1.The chairperson of the Keble shall be accountable to the kebele council, its execute committee, the woreda under whose Jurisdiction he/she falls and or the pertinent executive committee of the Urban council.

O. sub article 5 of article 90 of the constitution is hereby amended as follows:

5. submits periodic activity reports to the kebeles executive committee, its council, the woreda and or the urban councils' executive committee, not

390

390

302

ያቀርባል::

0. 1-የህገ መንግሥቱ አንቀጽ 90 ንዑስ አንቀጽ 6 ተሻሽሎ እንደሚከተለው ተሰተካክሏል::

6. እንደ አግባብነቱ በቀበሌው ፣ በወረዳው እና/ወይም በከተማው ምክቤቶችና ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎች የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል::

3- አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ የህገ - መንግሥት ማሻሻያ አዋጅ ከመስከረም 22 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ባህር ዳር
መስከረም 22 ቀን 1993 ዓ.ም
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክቤት

to mention that such report shall also be submitted to the resident public concerned

P. sub article 6 of article 90 of the constitution is here by amended and reformulated as follows:

6. Performs such other duties as maybe assigned to him /her by the kebele, woreda and urban councils and their respective executive committee, whichever maybe appropriate.

3. Effective date

This constitutional amendment proclamation shall come in to force as of the 2th day of October 2000.

Done at Bahir Dar
This the 2nd Day of October 2000
Council of the Amhara National Regional State

391

391